# የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀምን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 46/2013

Procedure Issued to Determine the Enforcement of Traffic Fines (Directive No. 46/2013)

የአዲስ አበባ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
Addis Ababa City Traffic Management Authority

መጋቢት 24፥ 2012

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ቁጥጥር እና የቅጣት አፈፃፀም ሂደት ወጥነት ባለው መልኩ እንዲከናወን የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ በዘርፉ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና አገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በተሻሻለው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009 የትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች በሚፈፅሙት ጥፋት ምክንያት የሚጠብቃቸው ቅጣት ከገንዘብ ቅጣት በተጨማሪ የጥፋት ነጥብ እንዲመዘገብ በማድረግ አሽከርካሪዎችን ለተወሰኑ ጊዜያት ከማሽከርከር ለማገድ የሚያስችል ስርዓት የዘረጋ በመሆኑ እገዳው የሚመራበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ደንብ ቁጥር 27/2002 አንቀፅ 5 መሠረት የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያቤት የትራፊክ ደንብን በማስፈፀም ሂደት ውስጥ ሊከተል የሚገባውን ስርዓት ያስቀመጠ ቢሆንም ዝርዝር አፈፃፀሙን በመመሪያ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀፅ 49(11) መሰረት የትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር እንዲያደርግ፣ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ደንብ ተላላፊዎች ላይ እርምጃ እንዲወስድ፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችን እንዲዘረጋ እና ተግባራዊነታቸውን እንዲያረጋግጥ በተሰጠው ስልጣን መሠረት በከተማችን ውስጥ የሚከናወኑ የትራፊክ ቁጥጥር ስራዎች ስርዓት ባለው መልኩ እንዲፈፀሙ የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም አሰራርን በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው በአዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 3 (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀም የአሰራር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የትራፊክ ቅጣት አፈፃፀምን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 46/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

1. "**ትራፊክ**" ማለት በማንኛውም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚሄዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡
2. "**ትራፊክ ተቆጣጣሪ**" ማለት የትራፊክ ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ እና የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ተብሎ ይከፈላል"፡፡
3. "**ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ**" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የትራፊክ ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው"፡፡
4. "**ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ**" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የትራፊክ ህጎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር በተለይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እንዲያረጋግጥና ከትራንስፖርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለመ ቆጣጠር አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፡፡
5. "**የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያቤቶች**" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህጎችን ለማስከበር ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ነው፡፡
6. "**ቅጣት**" ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ በመተላለፍ በተቆጣጣሪው አካል የሚወሰድ እርምጃ ነው፡፡

7. **“የቅጣት አፈፃፀም“** ማለት የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ በትራፊክ ተቆጣጣሪ የቅጣት ወረቀት ጽፎ ከመስጠት ጀምሮ ቅጣት ከፍሎ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ወይም ሰሌዳን እስከመረከብ እንዲሁም የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እስከማገድ ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ነው፡፡
8. **”የጥፋት ሪከርድ”** ማለት በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009(ማሻሻያ) መሠረት በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በጥፋት ላይ በመመስረት የሚመዘገብ ነጥብ ነው፡፡
9. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና 395/2009(ማሻሻያ) ማለት ነው፡፡
10. **”ፈቃድ”** ማለት አስቀድመው በነበሩ ህጎችም ሆነ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 1074/2010 መሠረት የተሰጠ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ነው፡፡
11. **”ፈቃድ ሰጪ አካል” ማለት** አግባብ ባለው ህግ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የመስጠትና የማደስ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡
12. **”የህክምና ማስረጃ”** ማለት ህጋዊ እውቅና ባለው የህክምና ተቋም በጠቅላላ ሀኪም ደረጃ የተሰጠ የትራፊክ አደጋ ተጎጅውን የጉዳት መጠን ወይም ሞት የሚገልፅ የሰነድ ማስረጃ ነው፡፡
13. **"በትራፊክ አደጋ የደረሰ ሞት"** ማለት ማንኛውም ሰው የትራፊክ አደጋ ደርሶበት በህክምና እርዳታ ላይ እያለ ሌላ ለሞት የሚያበቃ ምክንያት በመሀል ሳያጋጥመው በትራፊክ አደጋው መነሻነት ህይወቱ ካለፈ በትራፊክ አደጋው እንደሞተ ይቆጠራል፡፡
14. **ከባድ የአካል ጉዳት** ማለት ማንኛውም ሰው የትራፊክ አደጋ ደርሶበት በአደጋው ምክንያት ስራ ለመስራት ለመማር ወይም በሌላ በህይወቱ መስክ ላይ እክል የሚፈጥርበት ከሆነ ነው፡፡
15. **"የበአል ቀናት"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መደበኛ ስራ እንዳይሰራባቸው ሐይማኖታዊ እና ብሔራዊ በዓላት ናቸው፡፡
16. **“የከተማ ክልል”** ማለት የከተማ ምክር ቤት በቀጥታ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ወይም ከተማ ክልል ነው፡፡
17. **“አሽከርካሪ”** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው ሰው ነው፡፡

18. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፡፡

19. **"ባለስልጣን"** ማለት እንደየ አገባባቸው የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

20. **"የበላይ አመራር"** ማለት የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ማለት ነው፡፡

21. **"ዳይሬክቶሬት"** ማለት የመንገድ ትራፊክ ቁጥጥርና ኩነት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማለት ነው፡፡

22. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስጥ በሚያሽከረክሩ የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

**5. የመመሪያው አላማ**

የዚህ መመሪያ ዋና አላማ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎችን ተላልፈው በሚገኙ አሽከርካሪዎች ላይ የሚወሰደውን የእርምት እርምጃ ሂደት ግልፅ ማድረግና በጥፋት ላይ የተመሰረተ የጥፋት ሪከርድ አያያዝና አፈፃፀምን መወሰን ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የቅጣት አፈፃፀም አጠቃላይ መርህ

6. የትራፊክ ተቆጣጠሪው በቅጣት አፈፃፀም ወቅት ከዚህ በታች የተመላከቱ የቅጣት አፈፃፀም መርሆዎችን በጠበቀ ሁኔታ መተግበር ይኖርበታል፡፡

   1. ህግና ስርዓትን መከተል
   2. ከአድሎና ወገንተኝነት የፀዳ መሆን
   3. በጥፋት ላይ መመስረት
   4. ሰብአዊ ክብርን መጠበቅ
   5. ከብልሹ አሰራር የፀዳ መሆን
   6. በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ማረጋገጥ
   7. ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት
   8. በዘመናዊ ቴክኖሎጅ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት

## ክፍል ሶስት

## በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ የሚጣል ቅጣት አፈፃፀም

7. **በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ ስለሚጣል ቅጣት**

   በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት በዚህ መመሪያ እና ትራንስፖርትን ለመምራት በወጡ ህጎች ላይ በተቀመጠው የቅጣት አይነትና መጠን ላይ ብቻ በመመስረት ይሆናል፡፡

8. **በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ላይ እርምጃ ስለመውሰድ**

   1. የትራፊክ ተቆጣጣሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ የተላለፈን አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ጠይቆ በመቀበል በአንድነትና በነጠላ ላጠፋው ጥፋት የሚገባውን ቅጣት እንዲፈፅም የሚያዝ የቅጣት ወረቀት ወይም የማዘዣ ቁጥር ጽፎ ይሰጠዋል፡፡
   2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፎ የተገኘን አሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያልያዘ፣ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ በቦታው ያልተገኘ ወይም

በቅጣት ወረቀት እያሽከረከረ ያለ ከሆነ የተሽከርካሪውን የፊት ሰሌዳ ፈቶ በመያዝ የቅጣት ወረቀት ይሰጠዋል ወይም የአድራሻ ማሳወቂያ ወረቀት ያስቀምጥለታል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) በተጠቀሰው መሠረት የትራፊክ ተቆጣጣሪው ሰሌዳ ከመፍታት ይልቅ የተሽከርካሪውን ጎማ መቆለፍ የተሻለ መስሎ ከታየው የተሽከርካሪውን ጎማ በመቆለፍ የአድራሻ ማሳወቂያ ስቲከር ከአሽከርካሪው የበር እጀታ ላይ በመለጠፍ መሄድ ይችላል፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪውን የፊት ሰሌዳ ለመፍታት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ የኃላ ሰሌዳ ፈቶ በመያዝ ቅጣቱን እንዲፈፅም የቅጣት ወረቀት ፅፎ ይሰጠዋል ወይም የአድራሻ ማሳወቂያ ወረቀት ያስቀምጥለታል፡፡
5. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የትራፊክ ተቆጣጣሪው የቅጣት ወረቀት ከመስጠቱ በፊት የተጣሰውን የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ እንዲያርም አሽከርካሪውን ሊያዝ ይችላል፡፡
6. የትራፊክ ተቆጣጣሪው የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ከመፍታቱ በፊት የተሽከርካሪው ሞተር መጥፋቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡
7. የትራፊክ ተቆጣጣሪው በዚህ መመሪያ መሠረት በወሰደው እርምጃ አሽከርካሪው ባለመስማማት የቅጣት ወረቀት ፈርሞ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በቦታው ካልተገኘ የትራፊክ ተቆጣጣሪውን አድራሻ በማሳወቅ መሄድ አለበት፡፡
8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (7) መሠረት ለአሽከርካሪው የሚሰጠው ወይም እንዲቀመጥ የሚደረገው አድራሻ ይዘት የጥፋት አይነት፣ ጥፋቱ የተፈፀመበት ቦታ፣ ሰአት፣ ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት፣ የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር፣ የመስሪያቤቱን ስምና አድራሻ፣የተቋሙ ማህተም እና የተቆጣጣሪው ሙሉ ስምና ፊርማ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡
9. አሽከርካሪው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (7) መሠረት የተሰጠውን የአድራሻ ማሳወቂያ ፎርም በበአል ወይም የመንግስት ስራ የማይሰራባቸው ቀናት ካልሆነ በስተቀር በ12 ሰዓት ውስጥ በትራፊክ ተቆጣጣሪው መስሪያቤት ፊት በመቅረብ ወደ ቅጣት ደረሰኝ መቀየር አለበት፡፡

10. በዚህ አንቀፅ መሠረት የሚሰጠው የአድራሻ ማሳወቂያ ወረቀት ሰሌዳውን በፈታው ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በተቀበለው የትራፊክ ተቆጣጣሪ በራሱ የተፈረመበት መሆን አለበት፡፡
11. ትራፊክ ተቆጣጣሪው አሽከርካሪው በቦታው ባለመኖሩ የተሽከርካሪውን ሰሌዳ በመፍታት ላይ እያለ ወይም ፈቶ ከጨረሰ በኃላ ከቦታው ሳይርቅ አሽከርካሪው ከደረሰ እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን በመቀበል ሰሌዳውን መመለስ አለበት፡፡
12. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ በመተላለፍ የተፈታን የተሽከርካሪ ሰሌዳ የትራፊክ ተቆጣጣሪው መልሶ እንዲያስር አይገደድም፡፡

## 9. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ገቢ ስለማድረግ

1. የትራፊክ ተቆጣጣሪው በቁጥጥር ወቅት ከመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የተረከበውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ የመንግስት ስራ ዝግ በመሆኑ ካልሆነ በስተቀር በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከተው አካል ማስረከብ አለበት፡፡
2. የመስሪያ ቤቱ የቅጣት ኦፊሰር የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊው የተጣለበትን ቅጣት ፈፅሞ ሲቀርብ በትራፊክ ተቆጣጣሪው የተጣለው የቅጣት መጠን በተገቢው የቅጣት ሰብሳቢ አካል ገቢ መደረጉን በማረጋገጥ ለትራፊክ ህግ ተላላፊው የተያዘበትን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ይመልሳል፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪው ባለንብረት አሽከርካሪውን ማቅረብ ካልቻለ ተገቢውን የቅጣት ክፍያ በአሽከርካሪው ስም ፈፅሞ የአሽከርካሪውን አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኮፒ መረጃ እንዲሁም የተሽከርካሪው ባለቤት ስለመሆኑ የሚያስረዱ ሰነዶች ይዞ ሲቀርብ የተሽከርካሪው ሰሌዳ ይመለስለታል፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር የተያዘ ሰው ቅጣቱን ለመክፈል ካልቻለ በባለቤትነት ወይም በይዞታው የያዘውን ተሽከርካሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሌለው ሰው አሳልፎ የሰጠው ሰው

ቅጣቱን ጨምሮ መክፈል ሲችል ብቻ የተያዘበት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም የተሽከርካሪ ሰሌዳ ይመለስለታል ወይም የተቆለፈው የተሽከርካሪ ጎማ ይከፈትለታል፡፡

5. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪው ባለቤት የአሽከርካሪውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማቅረብ ባይችል በቂ ምክንያት ካለው በበላይ አመራር ውሳኔ እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡
6. በትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት አማካኝነት በዚህ መመሪያ መሠረት የትራፊክ ህግ በመተላለፍ ምክንያት የተያዘ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ደንብ ተላላፊው በቅሬታ ሂደት ላይ ካልሆነ በስተቀር በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ የሚጠበቅበትን ግዴታ በመወጣት መረከብ ካልቻለ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ለሰጠው አካል እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡
7. ተቆጣጣሪ መስሪያቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) መሠረት በመዘግየቱ ምክንያት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫው ፈቃዱ ወይም ሰሌዳው ለሰጪው አካል የተላለፈበት ደንብ ተላላፊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱንም ሆነ ሰሌዳ ሊያድስ ወይም በአዲስ መልክ ሊያገኝ የሚችለው የትራፊክ ህግ በመተላለፉ ምክንያት የተጣለበትን ግዴታ መወጣቱ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ለሰጪው አካል በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

**10. ቅጣትን ስለመፈፀም**

1. ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው ቅሬታ አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚከፈለው ቅጣት ኤጀንሲው ባዘጋጀው የትራፊክ ቅጣት መሰብሰቢያ ቦታ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ቅጣቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልከፈለ አሽከርካሪ ተጨማሪ ቅጣትና የጥፋት ሪከርድ ይያዝበታል፡፡
4. ቅጣቱን ፈፅሞ የቀረበ አሽከርካሪ በሌላ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ መተላለፍ የሚፈለግ ካልሆነ በስተቀር ቅጣቱን ለማስፈፀም በተቆጣጣሪ

መስሪያቤቱ የተያዘበት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይመለስለታል፡፡

5. የቅጣት ወረቀት ተፅፎ ከተሰጠ በኃላ የቅጣት ወረቀቱ የጠፋበት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊ የቅጣት ወረቀቱ ስለመጥፋቱ ከፖሊስ ማረጋገጫ ሲያቀርብ ቀሪ ደረሰኙ ኮፒ ተደርጎ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የጥፋት ሪከርድ ስለሚያዝበት ሁኔታ እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ

### 11. የጥፋት ሪከርድ ስለመያዝ

1. ማንኛውም አሽከርካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009 ሠንጠረዥ "ለ" እርከን 1 ከተዘረዘሩ ጥፋቶች በስተቀር በሌሎች እርከኖች የተቀመጡ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ ከገንዘብ ቅጣት በተጨማሪ የጥፋት ሪከርድ ይመዘገብበታል፡፡
2. ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ በመተላለፉ ምክንያት የተጣለበትን ቅጣት በወቅቱ ካልፈፀመ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 395/2009 ተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት እና የነጥብ ሪከርድ ይመዘገብበታል፡፡
3. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የጥፋት ሪከርድ ኤጀንሲው በሚያለማው የመረጃ ቋት መሠረት እንዲመዘገብ እና እንዲያዝ ይደረጋል፡፡
4. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ በሪከርድነት ተመዝግቦ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

### 12. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለማገድ

1. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ ከ17 እስከ 21 ሲደርስ ለ3 ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡

2. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ ከ22 እስከ 27 ሲደርስ ለ6 ወር የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡
3. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት የሚመዘገበው ነጥብ 28 እና በላይ ሲሆን ለ1 ዓመት አሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታገዳል፡፡
4. ከዚህ በላይ ባለው አንቀፅ መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታገደባቸው አሽከረካሪዎች የእገዳ ጊዜያቸውን ሲያጠናቅቁ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዳቸውን መልሰው ማግኘት የሚችሉት በባለስልጣኑ የሚሰጠውን የተሀድሶ ስልጠና እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ እንዲወስዱ ከተደረገ በኃላ ይሆናል፡፡
5. አንድ አሽከርካሪ በተለያየ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት በአንደኛው ምድብ ያለው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከታገደ በሌሎች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመጠቀም የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ማንኛውንም ተሽከርካሪ ማሽከርከር አይፈቀድለትም፡፡
6. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ስርዓት ተግባራዊ ከተደረገ በኃላ ባለስልጣኑ የተሀድሶ ስልጠና እና የአሽከርካሪ ማረጋገጥ ስርዓትን ተግባራዊ ያላደረገ ከሆነ ስርዓቱ እስኪጀመር ድረስ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ምክንያት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የታገደባቸውና የእገዳ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ አሽከርካሪዎች የተሀድሶ ስልጠናው በተጀመረ ጊዜ ስልጠናውን ለመውሰድ የውል ግዴታ ለኤጀንሲው እንዲገቡ በማድረግ ፈቃዳቸው እንዲመለስላቸው ይደረጋል፡፡

## 13. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ አፈፃፀም

1. ኤጀንሲው የጥፋት ነጥብ ሪከርዳቸው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲታገድ የሚያበቃ ደረጃ ላይ የደረሱ አሽከርካሪዎችን መረጃ በየጊዜው እየለቀመና አስፈላጊውን ማጣራት እያደረገ አሽከርካሪው እንዲያውቀው ካደረገ በኃላ በ 15 ቀናት ውስጥ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ከተያዘበት

የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም የስራ ክፍል በማስመጣት አያይዞ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለሰጠው አካል ለእገዳ ያስተላልፋል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዲታገድ ፈቃዱን ለሰጠው አካል ሲያስተላልፍ አሽከርካሪው በተለያየ ጊዜ የፈፀማቸው የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ዝርዝር እና የተመዘገበው ነጥብ ተሞልቶ ከአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ጋር ተያይዞ መላክ አለበት፡፡
3. ኤጀንሲው የእገዳ ማሳወቂያውን ፈቃዱን ለሰጠው አካል ካስተላለፈ በኃላ አሽከርካሪው ስለመታገዱ ማረጋገጫ ከፈቃድ ሰጪው አካል እንዲደርሰው ማድረግ እና በየጊዜው መከታተል አለበት፡፡
4. የእገዳ ማሳወቂያው የደረሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጪ አካል አሽከርካሪው የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ተቀያሪ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዳያወጣ መረጃው ከፋይሉ ጋር እንዲያያዝ ያደርጋል፡፡
5. የእገዳ ማሳወቂያው የደረሰው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሰጪ አካል አሽከርካሪው የእገዳ ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት በሌላ ምድብ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዳይጠቀም አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ አሽከርካሪው በሌላ ምድብ ያወጣው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ካለው እንዲታገድ ያደርጋል፡፡
6. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ የተደረገው ማናቸውም አይነት ጥፋት በመፈፀም የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጉ ምክንያት ከሆነ እገዳው የሚፈፀመው ምርመራውን ከያዘው የፖሊስ ተቋም መረጃው በደረሰ በ15 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) መሠረት እገዳ እንዲደረግ ከፖሊስ ተቋም ለኤጀሲው የሚላከው መረጃ ጋር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሀ. አደጋው የደረሰበት ቀንና ሰዓት፣

ለ. አደጋው የደረሰበት አድራሻ ክፍለ ከተማ፣ወረዳ፣ልዩቦታ፣

ሐ. አደጋውን ያደረሰው አሽከርካሪ ሙሉ ስምና አድራሻ፣እድሜ ፆታ

መ. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር

ሠ. ተጎጅው የሚታወቅ ከሆነ የተጎጂው ስምና አድራሻ፣ፆታ፣እድሜ፣

ረ. የጉዳቱን መጠን የሚገልፅ የህክምና ማስረጃ

## 14. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ መቆጠር የሚጀምርበት ጊዜ

1. የደንብ ተላላፊው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አሽከርካሪው ለእገዳ የሚያበቃውን የመጨረሻ ጥፋት ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እገዳው የሚፈፀመው ማናቸውንም ጥፋት ፈፅመው የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው ከሆነ የእገዳ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው አደጋው ከደረሰበት ቀን ወይም አጥፊው ከተያዘበት ወይም ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

## 15. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ጊዜያቸውን ስላጠናቀቁ አሽከርካሪዎች

1. የእገዳ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ደንብ ተላላፊዎች እገዳው ሲከናወን የተሰጣቸውን ደብዳቤ፣ እንዳስፈላጊነቱ የተሀድሶ ስልጠና እና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጥ የተሀድሶ ስልጠና ስለመከታተላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው በኤጀንሲው በመቅረብ እገዳው እንዲነሳላቸው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2. ኤጀንሲው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የእገዳ ይነሳልኝ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ (4) እና (5) የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ እገዳው እንዲነሳ ፈቃድ ለሚሰጠው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## 16. የይርጋ ጊዜ

1. ማናቸውም ደንብ ተላላፊ አሽከርካሪ ለእገዳ የሚያበቃውን የመጨረሻ ጥፋት ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት እስኪያልፍ ድረስ ከማሽከርከር ካልታገደ እገዳው በይርጋ ይታገዳል፡፡

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም እገዳው የሚፈፀመው ማናቸውንም ጥፋት ፈፅመው የሰው ህይወት እንዲያልፍ ወይም ከባድ የአካል ጉዳት እንዲደርስ በማድረጋቸው ከሆነ እገዳው በይርጋ የሚታገደው የወንጀል ተጠያቂነቱ በይርጋ በሚታገድበት ጊዜ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ከመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የሚጠበቅ ግዴታ

### 17. ከመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊ አሽከርካሪዎች የሚጠበቅ ግዴታ

1. የትራፊክ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፎ ሲገኝ የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የደንብ ተላላፊ የቅጣት ቲኬት ላይ መረጃዎችን በማስፈር እንዲፈርምበት ሲጠየቅ የመፈረም ግዴታ አለበት፣
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የቅጣት ወረቀቱን ፈርሞ የተቀበለ የትራፊክ ህግ ተላላፊ የቅጣት ወረቀቱን ፈርሞ በመቀበሉ ብቻ ጥፋቱን እንዳመነ አያስቆጥርበትም፣ ቅሬታ የማቅረብ መብቱንም አያስቀርበትም፡፡
3. ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፎ በመገኘቱ ምክንያት የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ ህግ ተላልፎ የተገኘዉን አሽከርካሪ ሲያሽከርክረዉ የነበረዉን ተሽከርካሪ የፊት ወይም የኃላ ሰሌዳ መፍታት ወይም የተሽከርካሪውን ጎማ መቆለፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰሌዳውን ለመፍታት ወይም ጎማውን ለመቆለፍ በሚወስደው እርምጃ እንቅፋት መሆን የተከለከለ ነው፤
4. ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፎ በመገኘቱ ምክንያት በትራፊክ ተቆጣጣሪዉ ለሚወሰድበት እርምጃ ፈቃደኛ ባለመሆን ሌሎችን ማሳደም የተከለከለ ነው፤
5. ማንኛውም አሽከርካሪ በትራፊክ ተቆጣጣሪው ላይ አምባጓሮ ማስነሳት የአሰራር ችግር መፍጠር ወይም መዝለፍ ወይም ማንቋሸሽ ወይም መሳደብ ወይም መዛት ወይም ማስፈራራት የተከለከለ ነው፤
6. የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ በትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የተሽከርካሪዉን የፊት ወይም የኃላ ሰሌዳ ለመፍታት አሽከርካሪዉን ከመሪ ላይ እንዲወርድ ወይም የተሽከርካሪዉን ሞተር እንዲያጠፋ ሲጠየቅ የመፈጸም ግዴታ አለበት፤

7. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ከታገደበት በኃላ ማንኛውንም አይነት ተሽከርካሪ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፤
8. የተሽከርከሪ ሰሌዳ ተገቢ ባልሆነ ቦታ ወይም እንዳይፈታ አድርጎ መበየድ ወይም በሪቤት ማሰር የተከለከለ ነው፤

## ክፍል ስድስት

## ከትራፊክ ተቆጣጣሪ ስለሚጠበቅ ግዴታ

### 18. ከቁጥጥር ባለሙያዎች የሚጠበቅ ግዴታ

በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ስነምግባር እና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ ለቁጥጥር ስራ ሲሰማራ ለስራው ከተቋሙ የተሰጠውን የደንብ ልብስ መልበስ እንዲሁም ማንነቱን የሚገልፅ የደረት ባጅ በማንጠልጠል በግልፅ እንዲታይ ማድረግ አለበት፣
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊውን ካስቆመ በኃላ ተገቢውን አክብሮት በመስጠት ራሱን በማስተዋወቅ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጠይቆ በመቀበል ጥፋቱን በግልፅ ማስረዳት አለበት፡፡
3. አሽከርካሪው የትራፊክ ህግ ተላልፎ ሲገኝ አሽከርካሪው ከተሽከርካሪው ሳይወርድና ሳይንገላታ የቅጣት ወረቀት ወድያውኑ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፣
4. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ስራ ሲያከናውን የትራፊክ ህግ ተላልፈው ክስ ለተፃፈላቸው፣የተሽከርካሪ ጎማ ለተቆለፈባቸው ወይም ሰሌዳ ለተፈታባቸው አሽከርካሪዎች የቅጣት ክፍያ የሚፈፅሙበትን ቦታ ማስረዳት እና የተያዘባቸውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወይም ሰሌዳ የሚቀበሉበትን ወይም የተቆለፈ ጎማ የሚከፈትበትን ቦታ መናገር አለበት፣
5. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ስራ ሲያከናውን አሽከርካሪው በሌለ ጊዜ ለሚፈታ የፊት ወይም የኃላ ሰሌዳ ወይም የተሽከርካሪ ጎማ መቆለፍ የዚህ መመሪያ አካል የተደረገውን የአድራሻ ማሳወቂያ ፎርም በመሙላት ለአሽከርካሪው ሊታይ በሚችል ቦታ ማስቀመጥ አለበት፣

6. ከትራፊክ ህግ ተላላፊ የተቀበለውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ፣ ከተሽከርካሪ የተፈታውን ሰሌዳ እና የተሽከርካሪው ጎማ የተቆለፈበት ቁልፍ በወቅቱ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ማስረከብ አለበት ፣
7. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህጎች ሲያስፈፅም ከአድሎ በፀዳ ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፡፡
8. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ለመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ሙያው የሚጠይቀውን አክብሮት ማሳየት፣ አለማመናጨቅ፣ አለመሳደብ፣ በማናቸውም ምክንያት አድሎ አለመፈፀም፣ በህግ ከተደነገገው ውጪ በተለይም ጥፋተኛ ባልሆነ ህግ ተላላፊ ላይ ቅጣት መወሰን የለበትም፡፡
9. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ ከመደበኛ የስራ ሰዓቱ ውጪ ያለ ተቋሙ እውቅና የትራፊክ ቁጥጥር ስራ መስራት የለበትም፡፡
10. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የመንገድ ትራንስፖርት ህግ የተላለፈውን አሽከርካሪ በተግባር ከፈፀመው ጥፋት በማሳናስም ሆነ በማስበለጥ መቅጣት የለበትም፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለቅሬታ አፈታት

### 19. ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 መሰረት የቅጣት ወረቀት የተሰጠውና በተሰጠው የቅጣት ወረቀት ተገቢነት ላይ ቅሬታ ያደረበት ማንኛውም ሰው ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅፅ መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

1. ቅሬታው የሚቀርበው በማዕከል ደረጃ ከሆነ የቅጣት ወረቀቱን ለሰጠው ወይም እርምጃውን ለወሰደው የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ቅሬታ ሰሚ ቅሬታውን በ2 ቀናት ውስጥ ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታው የሚቀርበው በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ ከሆነ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በ2 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት ለቀረበ ቅሬታ የሚመለከተው ኃላፊ በ1(አንድ) ቀን ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት ባቀረበው ቅሬታ ላይ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ወይም በተጠቀሰው ቀን ውስጥ ምላሽ ያላገኘ ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ለተቆጣጣሪ መ/ቤቱ የበላይ አመራር ውሳኔውን ባወቀ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት የተቆጣጣሪ መ/ቤቱ የበላይ አመራር ለቀረበው ቅሬታ በ2 ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት ያለበት ሲሆን በተቋሙ የበላይ አመራር ደረጃ የተሰጠ ውሳኔ በተቋም ደረጃ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለቅጣት

### 20. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ስለሚፈፅሙት ጥፋት

በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 17 ላይ የተቀመጡ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የሚጠበቅ ግዴታ የተላለፉ አሽከርካሪዎች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ "ሀ" መሠረት ቅጣት ይጣልባቸዋል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚጣለው ቅጣት አሽከርካሪው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ በመተላለፉ የሚጠብቀውን ቅጣት አያስቀርም፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የትራፊክ ተቆጣጣሪ ስለሚፈፅሙት ጥፋት

በሌሎች ህጎች የተቀመጡ የዲሲፕሊን ጥፋት በፈፀሙ የመንግስት ሠራተኞች ላይ የተጣሉ ግዴታዎች እና ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ግዴታዎችን የጣሱ የትራፊክ ቁጥጥር ባለሙያዎች በየተቋማቱ የስነምግባር መመሪያዎች በተቀመጡ ቅጣቶች መሠረት ይቀጣሉ፡፡

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**21. የመተባበርግዴታ**

ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመተባበር ግዴታ አለባቸዉ፡፡

**22. ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**23. መመሪያ ስለማሻሻል**

ይህን መመሪያ በሙሉ ወይም በከፊል በማንኛውም ጊዜ ኤጀንሲው ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**24. መመሪያው በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም**
**ጀሬኛ ሂርጳ ደበሎ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት አጀንሲ**
**ዋና ዳይሬክተር**

## ሰንጠረዥ ሀ

## የቅጣት ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የጥፋቱ ድግግሞሽና የቅጣት መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ጊዜ | ለሁለተኛ ጊዜ | ከሁለት ጊዜ በላይ |
| 1 | የትራፊክ ደንብ ተላልፎ ሲገኝ የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የደንብ ተላላፊ የቅጣት ቲኬት ላይ መረጃዎችን በማስፈር እንዲፈርምበት ሲጠየቅ ለመፈረም ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ያበላሸ፣ | 250 ብር | 350 ብር | 500 ብር |
| 2 | ማንኛውም አሽከርካሪ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህግ ተላልፎ በመገኘቱ ምክንያት የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ ህግ ተላልፎ የተገኘዉን አሽከርካሪ ሲያሽከርክረዉ የነበረዉን ተሽከርካሪ ሰሌዳውን ለመፍታት ወይም ጎማውን ለመቆለፍ በሚወስደው እርምጃ እንቅፋት የሆነ፣የተሽከርከሪ ሰሌዳ ተገቢ ባልሆነ ቦታ ወይም እንዳይፈታ አድርጎ የበየድ ወይም በሪቤት ያሰረ፣ | 300 ብር | 500 ብር | 750 ብር |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | የትራፊክ ተቆጣጣሪው ህግ የማስከበር ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት አምባጓሮ ያስነሳ፣ የአሰራር ችግር የፈጠረ ወይም የዘለፈ ወይም ያንቋሸሸ ወይም የተሳደበ ወይም የዛተ ወይም ያስፈራራ ማንኛውም አሽከርካሪ በወንጀል የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ | 500 ብር | 750 ብር | 1000 ብር |

ቅፅ 01

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ

-----------------ቅርንጫፍ/ፖሊስ መምሪያ

## የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች የአድራሻ ማሳወቂያ ቅፅ

ቀን--------------------------------

የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር------------------- የተሽከርካሪው አይነት-------------የጥፋት አይነት-----------------

ጥፋቱ የተፈፀመበት ክ/ከተማ----------ልዩ ቦታ--------------ሰዓት------------- የአሽከርካሪው ስም------------------

የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ------------- ----------------------የተቋሙ አድራሻ ልዩ ቦታ--------------------------ስልክ ቁጥር-------------------------

☐ የፊት ሰሌዳ ተይዟል ☐ የኃላ ሰሌዳ ተይዟል ☐ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተይዟል

☐ የተሽከርካሪ ጎማ ተቆልፏል ☐ ሊብሬ ተይዟል

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

ይህ የአድራሻ ማሳወቂያ ሰነድ የሚያገለግለው ለ12 ሰዓታት ብቻ ነው፡፡

ማህተም

ቅፅ 02

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ

-----------------ቅርንጫፍ

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳ ማሳወቂያ ቅጽ

ቀን--------------------------------

ለ-------------------------------አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር

ባስልጣን/መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ

---------------------------

ጉዳዩ፦ <u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እገዳን ይመለከታል፣</u>

የአሽከርካሪው ሙሉ ስም---------------------------------------የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር-------------------

የመንጃ ፈቃድ ቁጥር ---------------------- የመጨረሻ ጥፋት የተፈፀመበት ቦታ-------- ---------------------------------ቀን-----------------ሰዓት----------የጥፋት አይነት----------------- የጥፋት ነጥብ የደረሰበት ደረጃ---------------በዚህ መሠረት በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 በ395/2009 እንደተሻሻለ መሠረት በፈፀመው የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጥፋት ምክንያት ከ-----------------ቀን ጀምሮ ለ------------------------------- ጊዜ እስከ------------ቀን ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ የታገደ መሆኑን እያሳወቅን የአሽከርካሪው መረጃ የሚገኘው በቅ/ጽቤታችሁ በመሆኑ እገዳውን በመፈፀም ውጤቱን በግልባጭ እንድታሳውቁን እንጠይቃለን፡፡

<u>**ግልባጭ**</u>

- ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ
- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

  <u>**አዲስ አበባ**</u>

- ለትራፊክ ኦፕሬሽንና ደንብ ማስ/ቁጥ/ምክ/ዋና ዳይሬክተር
- ለትራፊክ ቁጥጥር እና ኩነት ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

  <u>**ት.ማ.ኤ**</u>

ቅፅ 03

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ**

**-----------------ቅርንጫፍ**

**የትራፊክ ህግ ተላላፊዎች ቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ**

**ቀን-------------------------------**

የቅሬታ አቅራቢው ሙሉ ስም--------------------------------------የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር--------------------

እርምጃ የተወሰደበት ቦታ --------------------- ቀን----------------ሰዓት----------የጥፋት አይነት-----------------

**የቅሬታው መነሻ በአጭሩ------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**የሚጠይቀው መፍትሄ/ዳኝነት-------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**------------------------------------------------------------------------------------------------**

**ቅሬታ አቅራቢው ፊርማ--------------------------------------**